<u>የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም።</u>
ሰሞሙን በኢትዮ-ሚድያ ታላቅ ህዝባዊ ጥሪ በሚል ርእስ የ«አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት» መሪዎች በቅርቡ ስለሚመጡ በቦታዉ ተገኝተን እንድንወያይ ለኢትዮጵያዉያን ጥሪ ተላልፋል። ጥሪዉን እናከብራለን ሆኖም ግን ተጋባዦች (ኢትዮጵያዉያን) ወደግብዣዉ ከመሄዳችን በፊት እራሳችንም ሆነ እንግዶችን መጠየቅ ያለብንን ጥያቄዎች ማዘጋዘት አለብን እንላለን።

አንደኛዉ ጥያቄያችን የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት መሪዎች እነማን ናቸዉ? ምንስ ለአገራችን የሚጠቅም ቁምነገር ይዘዉልን መጥተዋል የሚለዉን እንመልከት። መሪዎቹ እነ አቶ ገብሩ አስራት ከወያኔ ተለየን ብለዉ በተደጋጋሚ እንደነገሩን ከሆነ ወያኔን በአሁኑ ጊዜ የሚመሩት (መለስ,በረከት,ስዩም,ስብሃት,ሳሞራዉ እንዲሁም ሌሎች) አፍቃሪ ኤርትራ ስለሆኑ በትዉልድም ሆነ በጋብቻም ከኤርትራ ጋር የተሳሰሩ ስለሆኑ ኢትዮጵያን እየጎዱ ኤርትራን ይጠቅማሉ ስለዚህ በዚህ ልዩነታችን ከወያኔ ተለይተናል ይሉናል።

ይህ ቡድን (አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት) በተለይ በከሀዲነት ከሚወነጅሉት ዋነኛዉ መለስ ዜናዊ ነዉ። ይሁን ይህንን እንደወረደ እንቀበለዉ እናንተስ እነማን ናችሁ ብለን ለምንጠይቃቸዉ ጥያቄ መንደርደሪያ እንዲሆነን ከስማቸዉ እንነሳ። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ዉስጥ የሚንቀሳቀሱት ድርጅቶች አንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ወይም የመላዉ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ብለዉ ከወያኔ ጋር እየታገሉ እናንተ አረና ትግራይ ከምትሉ ለምን አረና ኢትዮጵያ አትሉምና ለትግራይ ጥቅም ከምትታገሉ ለኢትዮጵያ ጥቅም አትታገሉም ብለን እንጠይቃለን።

ሁለተኛዉ ጥያቄያችን ደግሞ የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት መሪዎች በተለያየ አገጣሚ ተጠይቀዉ መልስ እንደሰጡትና አንዳንድ ፍንጮች እንደሚያመለክቱት አሁንም አንቀጽ 39 የሚባለዉን እስከመገንጠል የሚል «ህገ መንግስት» እንደሚደግፉ ገልጸዉልናል። አሁንስ በዚሁ አቋማችሁ ጸንታችኋል ወይስ የተለየ ነገር አለ ብለን እንጠይቃለን። አንቀጽ 39 የሚባለዉን እስከመገንጠል የሚል «ህገ መንግስት» እንደማይፍም ካሉንና ከአረጋገጡልን እሰየዉ ድጋፋችን ያገኛሉ ከሌሎች ጋር ለኢትዮጵያ አንድነት አብረዉ እንዲሰሩ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን። ይህ ካልሆነ ግን በድሮዉ በአረጀና በወደቀ እስከመገንጠል በሚለዉ አቋማቸዉ የሚቀጥሉ ከሆነ ግን አንድ አንድ የምንነግራቸዉ ነገሮች አሉ።

እንደሚታወቀዉ በ70 ዎቹ መጨረሻና በ80 ዎቹ በአለም ላይ ያሉ የግራ ክንፍ አብዮት አራማጆች (ኢትዮጵያዉያንን ጨምሮ) የብሄርና የብሄረሰቦች መብት እስከመገንጠል የሚል ፍልስፍና ያራምዱ ነበር። አሁን ግን የአለም ሁኔታ ተቀይሯል። ኢትዮጵያዉያን የግራ ክንፍ አብዮት አራማጆችም (የኢህአፓና የመኢሶንን መሪዎችን ጨምሮ) ከተለወጠዉ አለም ጋር እራሳቸዉን በማስተካከል እስከመገንጠል የሚለዉ ፍልስፍና አገር አፍራሽ መሆኑን በመገንዘብ አንድነት በሚሉበት በአሁኑ ጊዜ እናንተን አንቀጽ 39 እና እስከመገንጠል ብላችሁ የሙጥኝ ያላችሁበት ሚስጥሩ ምንድነዉ ንገሩን ብለን ልንጠይቃችሁ ተዘጋጅተናልና መልሳችሁን ከዚሁ አዘጋጁ እንላለን።

ከላይ ከተጠቀሰዉ ጋር ተያያዥነት ያለዉ ነገር ቢኖር የጎሳ ክልል ነዉ። በተለያየ አጋጣሚ ተጠይቃችሁ ቀጥተኛ መልስ ሳትሰጡበት አልፋችኋል። አሁን ግን ቀጥተኛ መልስ እንፈልጋለን ይኸዉም በድርጅታችን ኢትዮጵያ ዉስጥ ያለዉን የጎሳ ክልል እናምንበታለን ወይንም አናምንበትም የሚል መልስ ነዉ የምንፈልገዉ።

ሶስተኛዉ ጥያቄያችን ደግሞ ድርጅታችሁ (አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት) በተለያየ አጋጣሚዎች እንደገለፀዉ ኢትዮጵያ የባህር በር እንደሚያስፈልጋትና ይህ እንዳይሆን ግን የነመለሰ ዜናዊ ቡድን እንቅፋት እንደሆነባችሁ ይናገራል። ይህን

በሚመለከት ሁለት ነገሮች እንድታብራሩልን እንፈልጋለን። የመጀመሪያዉ ጥያቄያችን የኢትዮጵያን እጣ ፈንታ ደደቢት በርሃ ላይ ወያኔ ሲወስን (አሰብን ለኤርትራ መስጠትን ጨምሮ) እናንተ (አረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት) መሪዎች በወያኔ አመራር ላይ ነበራችሁ። ያኔ ይህንን ጉዳይ ለምን አላነሳችሁም? ሁለተኛዉ ስጋታችን ደግሞ አሰብን ከኤርትራ ላይ በዉድም ሆነ በግድ መዉሰድ አለብን ስትሉን ብዙ ህይወትና ንብረት ከተገበረ በኋላ አሰብን ማን ሊጠቀምበት? የኢትዮጵያ ህዝብ ወይንስ አንቀጽ 39 እና እስከመገንጠል ብላችሁ የሙጥኝ ያላችሁበት ሚስጥር ወደፊት የምትገነጠለዉ ታላቂ ሪፓብሊክ ትግራይ?

መልሳችሁ ሁለተኛዉ ከሆነ የኢትዮጵያን ህዝብ ለሁለተኛ ጊዜ አታሞኙትም እንላለን። ይህንን ስንል ማለት የፈለግነዉ ትግራይ በሻቢያ ስትወረር አገራችን ተደፈረች ብላችሁ ላቀረባችሁት ጥሪ ፈጥኖ ለደረሰዉ የኢትዮጵያን ህዝብ ከወያኔ የተሰጠዉን ወሮታ በምርጫ 97 ማግስት አይተነዋል። አሁንም የኢትዮጵያን ህዝብ አሰብን ከኤርትራ ላይ ለመዉሰድ ከተማገደ በኋላ አሰብ የትግራይ የግል ንብረት ስለሆነች ሌላዉ ኢትዮጵያዊ ለትግራይ የወደብ ግብር ይክፈል እንዳይባል እንሰጋለን።
ይህንን ካልን በኋላ ስጋታችንና ህልማችን ልንጋራችሁ እንፈልጋለን።

ስጋታችን፤ ወያኔ ሀርነት ትግራይም ሆነ አረና ትግራይ አንድ ነገር ያመሳስላቸዋል። ይኸዉም ትግራይ የሚለዉ ቃልና አላማ። ትግራይ ትግራይ ስትሉን ለሌላዉ ህዝብና ለኢትዮጵያ ደንታ የሌላችሁ ይመስለናል። አሁንም እንደድሮዉ በወጣትነት ዘመናችሁ ከአእምሮአችሁ ዉስጥ የገባዉ የጎጠኝነት ስሜት የለቀቃችሁ አይመስለንም። ምክንያት ቢባል ይህንን አመለካከታችን የሚያስለዉጥ ተግባር አላየንባችሁም። ትናንትም ትግራይ ትግራይ ስትሉን ነበር ዛሬም ትግራይ ትግራይ ትሉናላችሁ። ስጋታችን በዚህ አያቆምም ሰፋ አድርገን ስንመለከተዉ ታላቋ ትግራይ የሚለዉ ቅዠት የለቀቃችሁ አይመስለንም። እኛን ከሁሉም የሚያስፈራን በኢኮኖሚና በወታደራዊ ሀይል የዳበረችና የአሰብን ወደብ የያዘች ታላቋ ትግራይን ከያዛን በኋላ አንቀጽ 39ን ተጠቅመንና ህጋዊነትን ሰጥተን እንገነጥላለን የሚለዉን አላማችሁን አሁንም የያዛችሁት ይመስለናል። ስጋታችንን በትንሹ ከጠቆምናችሁ በኋላ ህልማችን ደግሞ እንጋራችሁ።

ህልማችን፤ ኢትዮጵያዊነት ፍቅር ነዉ፤ ኢትዮጵያዊነት ክብር ነዉ፤ ኢትዮጵያዊነት ኩራት ነዉ፤ እኛ ኢትዮጵያዉያን ከተባበርንና ከተማመን አገራችንም ታድጋለች ወገናችንም ከድህነት ይለቀቃል። መገንጠል ለማን ጠቀመ? ከ17 አመት በፊት የተገነጠለችዉ ኤርትራ ብዙ ህልም ነበራት። በአሁኑ ጊዜ ኤርትራ በምን ሁኔታ ላይ እንደምትገኝ ሁላችንም የምናዉቀዉ ነዉ። እስኪ የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት መሪዎች ከትግራይ ድርጅቶች ዉስጥ የመጀመሪያዉ ፋና ወጊ ይሁንና በዚህ ስብሰባ ላይ የጎሳ ክልል ይፍረስ፤ እስከመገንጠል የሚለዉ «ህገ መንግስት» አገር አፍራሽ ስለሆነ መሻሻል አለበት ብላችሁ በድፍረት ተናገሩ። ይህንን የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት መሪዎች ካደረጋችሁ ኢትዮጵዊነታችን የኩራት የፍቅርና የመተማመን ይሆናል። ይህንን ስብሰባ እንደ ታሪክ አጋጣሚ ተጠቅመን አገራችንና ህዝባችንን እንታደጋቸዉ። ሞታችንም ድነታችንም አንድ ላይ ነዉ። ሌላዉ ኢትዮጵያ ተርቦ ትግራይ ብቻዋን አትጠግብም። ሌላዉ አካባቢ ፈርሶ ትግራይ ብቻዋን አትተርፍም - አንላቀቅም። ለዚህ ነዉ ሞታችንም ድነታችንም አንድ ላይ ነዉ የምንለዉ።

በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር መጥቀስ እንፈልጋለን። አንድ የቅንጅት ከፍተኛ አመራር በምርጫ 97 ጊዜ ስለ «ህገ መንግስቱ» አስተያየት እንዲሰጡ በተጠየቁ ጊዜ «የወያኔ ህገ መንግስት ከተጻፈበት ወረቀት በላይ ዋጋ አያወጣም። ቅንጅት በህዝብ የድምጽ ብልጫ ከተመረጠ ብዙ መሻሻል ያለበት ነገር አለ » ብለዉ ሳይፈሩ በድፍረት በኢትዮጵያ ቴሌቪዢን ተናግረዋል። ኢትዮጵያዊነት ማለት ይኸንን ያህል መስዋትነት ይጠይቃል። ብዙዎቻችን በአማካይ እድሜ ላይ እንገኛለን። ከአሁን በኋላ ምን ያህል ጊዜ እንዳልኖርን ነዉ? ምንም እንኳ የኛ ትዉልድ ጥሩ ነገር ያለገኘ እድሜዉን በጦርነት፤ በስደት፤ በእስራት የአሳለፈ

ትዉልድ ቢሆንም ቢያንስ እንኳ ለልጆቻችን በሰላም እንዲኖሩ መሰረት ጥለንላቸዉ እንለፍ። ፍቅርንና መተማመንን ለልጆቻችን እናሳያቸዉ። ህልማችን እዉን እንዲሆን እግዚአብሄር ይርዳን።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በብዙ የተቃማዊ ሀይሎች (አረና ትግራይን) ጨምሮ አንድ በሰፋት የሚነገር ነገር አለ። ይኸዉም የመለሰ ዜናዊ ከስልጣን መወገድ ለኢትዮጵያ ወቅታዊ ችግር ሁሉ መፍትሄ እንደሆነ መነገሩ ነዉ። የመለሰ ዜናዊ ከስልጣን መወገድ ለችግራችን አንዱ መፍትሄ ነዉ። ብቻዉን ግን መፍትሄ አይደለም እንለላለን። አንድን አምባገነን በሌላ አምባገነን መተካት ምንም መፍትሄ እንደማያመጣ የኢትዮጵያ ህዝብ ከተረዳዉ 17 አመት አስቆጥሯል። ደርግ በወያኔ በመተካቱ የኢትዮጵያ ህዝብ ምን ተጠቀመ? እስኪ እንመልከት፤ ወያኔ ደርግን እንደተካ «ጦረኛዉ ደርግ አገሪቱን በጦርነት ዉስጥ ስልከተታት ኢትዮጵያ ደኸ አገር ሆነች። ሰዎችን ያለፍላጎታቸዉ ሰፈራ እያለ ያሰፍራል» ብሎ ወነጀለ።

ከበሮ በሰዉ እጅ ሲያዩት ያምር ሲይዙት ይደናገር ማለት ይኸ ነዉ። ደርግ ኢትዮጵያን ላለማስደፈር ከተዋጋቸዉ ሀይሎች ጋር ወያኔ በጦርነት ዉስጥ ተጠምዶ ይገኛል። ደርግ ከሻቢያ፤ ከኦነግ፤ ከሶማሊያ፤ ከኦብነግ ጋር ተዋግቷል። ወያኔ ከነዚህ ሀይሎች ጋር ሁሉ በመዋጋት ላይ ይገኛል። ወያኔ ሰዎችን ያለፍላጎታቸዉ ሰፈራ እያለ ያሰፍራል።
እናስ ለአገራችን ችግር <u>መፍትሄዉ ምንድን ነዉ ቢባል ዲሞክራሲ ብቻ ነዉ። በህዝብ የተመረጠ መንግስት ብቻ ነዉ ኢትዮጵያን ከገባችበት ማጥ የሚያወጣት እንላለን።</u> በምርጫ 97 ጊዜ የቅንጅት አመራር ያስቀመጧቸዉ ስምንት ነጥቦች ለዲሞክራሲ ስርአት ወሳኝ ስለሆኑ ዛሬም ተግባራዊ መሆን አለባቸዉ እንላለን።

በኢትዮጵያ ተማሪዎች አስተባባሪነት የተቀጣጠለዉን ህዝባዊ አመጽ ለማስታገስ የዘዉዱ ስርአት ከወሰዳቸዉ እርምጃዎች አንዱ የጠቅለይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀአብተወልን ካቢኔ በልጅ እንዳልካቸዉ እምሩ ካቢኔ መተካት ነበር። የህዝቡ መልስ ግን «የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም» የሚል ነበር። የልጅ እንዳልካቸዉ እምሩ ካቢኔ ደግሞ ህዝባዊ አመጽን መቋቋም ሲያቅተዉ ህዝቡ አሁንም «ነጭ አህያ ቢሄድ ነጭ አህያ መጣ አዲሱ ካቢኔ ዝርጥርጡ ወጣ» ነበር መልሱ። ታሪክ እራሷን ትደግመልች እንዲሉ እኛም ዛሬ የጉልቻ መለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም እንላለን። የኢትዮጵያ ህዝብ የሚፈልገዉ በህዝብ የተመረጠ መንግስት እንጅ የግለሰብ ለዉጥ አይደለም።

እንግዲህ ለነዚህ ዉይይቶች መልስ የአረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት አመራር ተዘጋጅቶ እንዲመጣ ይህች ጽሁፋችን እንደምንም ተሸሎክልካ ትድረሳችሁ። ለማንኛዉም የአዳራሹን ሙቀት እንድትችሉት ምኞታችን እንገልጻለን። መልካም ዉይይት።

የጎሳ ክልል ይፍረስ!
ኢትዮጵያዊነት ለዘላለም ይኖራል!

በዋሽንግተን ዲሲና በርጂንያ አካባቢ ኗሪ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት።

EthioLion.com